የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 53
ADDIS ABABA,31st July, 2015

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፱፻፩/፪ሺ፯ ዓ.ም**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በናይጄሪያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ.....................................ገጽ ፰ሺ፪፻፸

**CONTENTS**

Proclamation No. 901/2015

The Agreement on the Establishment of Joint Ministerial Commission between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Federal Republic of Nigeria Ratification Proclamation ...........................................…………………........Page 8270

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፩/፪ሺ፯

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በናይጄሪያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የጋራ ሚኒስትሮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በናይጄሪያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ስምምነት ሚያዚያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 901/2015

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON THE ESTABLISHMENT OF A JOINT MINISTERIAL COMMISSION BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL REPUBLIC OF NIGERIA**

WHEREAS, the Agreement on the Establishment of a Joint Ministerial Commission between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Federal Republic of Nigeria was signed in Addis Ababa on the 29th day of April, 2006;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 25th day of June 2015;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በናይጀሪያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፩/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በናይጀሪያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሚያዚያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

፫. **የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንን ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as "the Agreement on the Establishment of Joint Ministerial Commission between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Federal Republic of Nigeria Ratification Proclamation No. 901/2015''.

2. **Ratification of the Agreement**

The Agreement on the Establishment of a Joint Ministerial Commission signed in Addis Ababa on the 29th day of April, 2006 between the Federal Democratic Republic of Nigeria, is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Foreign Affairs**

The Ministry of Foreign Affairs is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 31st day of July, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**